# ሲድኒ ሼልደን



# የፍርድ ቀን ዘመቻ

ትርጉም ብስራት አጥላባቸው

@BOOKALEM

# ሲድኒ ሼልደን

# የፍርድ ቀን ዘመቻ

በዓብዓለም በቴሌግራም የቀረበ መጽሐፍ
@BOOKALEM
ይቀላቀሉን

Sidney Sheldon
The Doomsday Conspiracy

ትርጉም– ብሥራት እጥላበቸው ኃይሌ

ሰኔ 2013 ዓ.ም



@BOOKALEM

"በሚያጓጓ ጊዜ ውስጥ ያኑርህ!"

(ጥንታዊ የቻይናዎች ርግማን)

<u>መታሰቢያ</u>

ለወይዘሮ ጽጌ ኃይሌ ደስታ


አንደኛ እትም– ሐምሌ 1986 ዓ.ም
ሁለተኛ እትም–ግንቦት 1998 ዓ.ም
አሥራ አንደኛ እትም–ሰኔ 2007 ዓ.ም


<u>ሌሎች ሥራዎች</u>

አፐሬሽን መቅደላ– ድርሰት
ሌላው ገጽታዬ– ሲድኒ ሼልደን
ዓልተኛው– ጀምስ ፓተርሰን
ተለዋጭ ሰላይ– ፍሬደሪክ ፎርሲዝ
ግዙፍ የስኬት እርምጃዎች– አንቶኒ ሮቢንስ
የስኬት ጉዞ–

<u>በቅርብ የሚወጡ</u>

የቢይሩቱ ፍንዳታ -ድርሰት
ሞሳድና ዘመቻ ሙሴ– እውነተኛ ታሪክ
የዘመናት እንቆቅልሽ– ዘጋቢ
ጠቢባ የወሲብ መምሕርት-ሥነ-ወሲብ
የሕልም መፍቻ ከትርጉሙ
ብስል ጥቅሶች



@BOOKALEM

# ከፍል አንድ
## አዳኙ

እሁድ ጥቅምት አሥራ አራተኛ ቀን
2100 ሰዓት
አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ኤንአስኤ. ለ–ኮምሲክ ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
መልዕክት– ይጀመር
አስታውቁ ለፈረንሳይ፤ ጣሊያን፤ ጀርመን፤ ስዊዘርላንድ፤ እንግሊዝ፤
ካናዳ፤ ሩሲያ የመረጃ ድርጅቶች።

---

<u>እሁድ ጥቅምት አሥራ አራተኛ ቀን</u>
<u>አስቸኳይ መልዕክት</u>
<u>በጣም ከፍተኛ ምሥጢር</u>
ኤን. ኤስ.ኤ ለ–አሥራ ሰባተኛው ቀጣና የባሕር ኃይል መረጃ ጽሕፈት ቤት
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
አርእስት–ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ
ወደ ኤጀንሲው በጊዜያዊነት እንዲዛወር አስፈላጊው ሁሉ ይዘጋጅ።
ወዲያውኑ ተግባራዊ የሚሆን፤
ከላይ በተጠቀሰው ላይ የምታደርጉት ትብብር ይጠበቃል።


@BOOKALEM

## ኦተንዶርፍ ሰዊዘርላድ

## እሁድ ጥቅምት አሥራ አራተኛ ቀን

## 1500 ሰዓት

እማሰኩ ጠርዝ ቆመው የነበሩት ምስክሮች ሽብር በተሞላበት ፀጥታ ደንዘዘውና አፍጥጠው እየተመለከቱ ነበር። አፈታቸው የተጋደመው ትዕይንት አስቂኝ የሆነ ብልሹ ቅርጽ ያለው ከጥንታዊው ሰው ጥልቅና ጨለማ ገና ያልበሰለ ሕሊና ውስጥ የተበተነ ቅዠት ነበር። እያንዳንዱ ምስክር የተለያየ የስሜት መለዋወጥ ነበር የደረሰበት። አንዱ ሕሊናውን ስቶ ወደቀ። አንድ ሌላ ሰው አስመለሰው። አንዷ ሴት ከቁጥጥር ውጭ ሆና ትንዘፈዘፍ ነበር። ሌላ ሰው ደግሞ ‘የልብ ድካም ሊይዘኝ ነው’ ሲል አሰበ። አዛውንቱ ካህን ደግሞ መቁጠሪያቸውን ጨምድደው ያዙና አማተቡ። “አባት ሆይ እርዳኝ! ሁላችንንም እርዳን! ከዚህ ሰው ከመሰለ እርኩስ መንፈስ ተከላከልልን። በመጨረሻም የሰይጣኑን መልክ ተመልክተናልና። ይህ የዓለም መጨረሻ ነው። የዳኝነት ቀን መጥቷል። የፍጻሜው ጦርነት እዚህ ነው። እርማጌዶን! እርማጌዶን! እርማጌዶን!”...



@BOOKALBM

# ምዕራፍ ሦስት

## ኢታዋ ካናዳ 2400 ሰዓት

የምሥጢር (ኮድ) መጠሪያው ጁኑስ ይባላል። በከፍተኛ ደረጃ የተጠናከረ የፀጥታ ጥበቃ በሚደረግለት አንድ ወታደራዊ ጦር ሰፈር በሚገኝ አዳራሽ ውስጥ ለተሰበሰቡ አሥራ ሁለት ሰዎች ማብራሪያ እየሰጠ ነው።

"ሁላችሁም እንደተነገራችሁ "'የፍርድ ቀን ዘመቻ'" ተጀምሯል! በከፍተኛ ፍጥነትና በጥብቅ ምሥጢር ተፈልገው መገኘት ያለባቸው የዐይን ምስክሮች አሉ። ሊደርስ በሚችል የምሥጢር መባከን ምክንያት በተለመደው የሰለላ መዋቅር ለመጠቀም አልተቻለም።"

"ለመሆኑ ለዚህ ሥራ የምንጠቀምበት ሰው ማነው?" ግዙፍና ትዕግስት የለሽ የሆነ ሩሲያዊ።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ይባላል።"

"ኮማንደሩ የተመረጠው እንዴት ነው?" ጨካኝና የገርነት ሥልጣን የሚታይበት ጀርመናዊ።

"ኮማንደሩ የተመረጠው የሲ.አይ.ኤ. የኤፍ.ቢ.አይ እና የሌሎችም ከግማሽ ደርዘን በላይ የሚሆኑ የስለላና የመረጃ ድርጅቶች የኮምፒውተር ፋይል ፍተሻ ከተደረገበት በኋላ ብቃቱ ስለታመነበት ነው።"

"እባክዎን የሰውየው ብቃትና ችሎታ ምን እንደሆነ ለመጠየቅ እችላለሁን?" ትሁትና ምሥጢራዊ የሆነው ጃፓናዊ።

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ በመስክ ሥራ ከፍተኛ የሆነ ልምድ ያለውና ስድስት የተለያዩ ቋንቋዎችን አጣርቶ እንደ ተወላጆቹ ለመናገር ከመቻሉም በላይ መረጃን ፈልፍሎ የማውጣት ብቃቱን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሕይወት የሚገኝ ምንም የሥጋ ዘመድ የለውም።"

"የጉዳዩን አስቸኳይነትስ ተገንዝቧል?" አደገኛውና ንቀት የሚታይበት እንግሊዛዊ።

"አዎን! ሁሉንም ምስክሮች በአስቸኳይ አድኖ የማግኘቱን ጉዳይ ተረድቶታል። ይጠበቅበታልም።"

"የተልዕኮውን ተግባርስ ተረድቷል?" ጨቅጫቃና ደረቅ ፈረንሳዊ።

"የለም አልተረዳም።"

"ምስክሮቹን ፈልጎ ካገኛቸው በኋላስ?" ትዕግስተኛና ቀልጣፋው ቻይናዊ።

"ጣፋጭ የሆነ ሽልማት ይሸለማል!" ሲል ጁኑስ ጥያቄና መልሱን ደመደመ።



BOOKALEM

"በአጠቃላይ ምንም አታስታውስም?"

"ጥቁር ካፖርት ለብሶ ነበር።"

"አቶ ቤከርማን አንድ ውለታ እንድትውልልኝ እፈልጋለሁ ። ከኔ ጋር ወደ ሎተንዶርፍ ብትጓዝስ?"

"ይህ የእረፍት ቀኔ ነው። ሥራ በጣም......"

"በደስታ እከፍልሃለሁ።"

ቤከርማን ማሰብ ጀመረ። 'ለምን አልሄድም? በመኪና ለመጓዝ ቀኑም ደስ የሚል ነው። አይደለም?'

ውቦቹን የኢመንዝ፣ ሜከንና ሉዛን መንደሮችን እያቋረጡ ወደ ደቡብ ተጓዙ። መንገድ ላይ የሚታየው የተፈጥሮ ውበት ትንፋሽ የሚያሳጥር አድናቆት ቢያሳድርም በሮበርት አዕምሮ ውስጥ ግን ሌሎች ብዙ ጉዳዮች ነበሩ። ሳርነን እና ብሩኒግ የተባሉ መንደሮችን አቋርጠው እንደተጓዙ "ምን ያህል ይቀረናል?" አለ ሮበርት።

"ቶሎ እንደርሳለን" ሲል ቤከርማን ቃል ገባለት። "የሚቀጥለው ከተማ ቱን ይባላል። እሱን አለፍ ካልን ደረስን ማለት ነው።"

የሮበርት ልብ መዝለል ጀመረ። አንድ ከግምት በላይ ስለሆነ ነገር ከሌላ ሥርዓተ–ከዋክብት ዓለም ስለመጡ ያልታወቁ ጐብኚዎች ሊመሰክር መቃረቡ ተሰማው።

ቱን ከተማን አቋርጠው ትንሽ እንደተጓዙ ቤከርማን ወደ አንድ አቅጣጫ በእጁ እመለከተና......"እዚያ አካባቢ ነው!" ሲል ተናገረ።

ሮበርት መኪናውን ቀዝቀዝ አደረገና ከመንገድ ዳር አቆማት።

"አውራ ጎዳናውን ተሻግሮ ከዛፎቹ በስተኋላ!" ሲል ቤከርማን ተናገረ። ሮበርት በውስጡ የመጓጓትና የመነሳሳት ስሜት ተሰማው። "እስቲ እንመልከት!" አለና መንገዱን ጀመረ።

አንድ የጭነት መኪና አሳልፈው መንገዱን ከተሻገሩ በኋላ ሮበርት ሾፌሩን ተከትሎ ዛፎች ወዳሉበት ከፍ ያለ ሥፍራ አመራ።

ከሥፍራው ሲደርሱ ፊታቸው የተጋደመው የአየር ንብረት ባሉን ክስካሽ ብቻ ነበር!



@BOOKALEM.

"213 ኤ.ግሩ-ሸ ጎዳና ቀይት ቻፕል ለንደን ምሥራቅ -3-" አለችና ተና ብላ ሮበርትን እየተመለከተች "ይህን ጉዳይ በተመለከተ ኩባንያችን በሕግ እንደማይጠየቅ እርግጠኛ ነህ?" አለችው።

"ቃሌን እሰጣለሁ!" አለ ሮበርት። "የኔና የማዘርቬድ የግል ጉዳይ ነው።" ኮማንደር ቤላሚ በሚቀጥለው የስዊስ ኤር አውሮፕላን ወደ ለንደን ተጓዘ።

---

በጨለማው ክፍል ውስጥ ብቻውን ተቀምጦ ያወጣው እቅድ ምን ያህል እንከን የለሽ መሆኑን በጥሞና እየመረመረ ነበር። በዚህ ወቅት ከሰጠመበት የሐሳብ ባሕር በስልኩ ተቀሰቀሰ።

"ጃኑስ ነኝ!" አለ ስልኩን አንሳና።

"ጃኑስ ጀኔራል ሒሊያርድ ነኝ!" አለ ደዋዩ።

"ቀጥል።"

"ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምስክሮች አግኝቷል።"

"በጣም ጥሩ! አስፈላጊውን ጉዳይ በአስቸኳይ አስፈጽም።"

"እሺ ጌታዬ!"

"ኮማንደሩ አሁን የት ነው የሚገኘው?"

"ወደ ለንደን በመጓዝ ላይ ነው። ሦስተኛውን ምስክር በአጭር ጊዜ ውስጥ ያገኘዋል እላለሁ።"

"ጥሩ! እኔም ኮማንደሩ ስለደረሰበት ዕድገት ለኮሚቴው አሳውቃለሁ። በተጨማሪም የዚህ ዘመቻ ምሥጢራዊነት የተጠበቀ ሆኖ ይቀራል።"

"ይገባኛል ጌታዬ። የማቀርበው ሐሳብ......"

የስልኩ መስመር ተዘጋ።

---

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ቡንዴሳን ዋልተስቻፍት
ምክትል ዳይሬክተር ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም።
እርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

1. ሐንስ ቤከርማን – ካፔል
2. ፍሪትዝ ማንዴል – በርን።

የመልዕክት መጨረሻ



@BOOKALEM

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ከኡተን ዶርፍ ሃምሳ ማይሎች ራቅ ብሎ የሊጀንፊልድ ቤተሰብ ሊሊት ባልተለመደ እንግዳ ነገር ሲረበሽ ነበር ያደረው። ተለቅ ያለው ህፃን ልጅ በመኝታ ቤቱ መስኮት የገባ የሚብረቀረቅ ቢጫ መብራት ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ሁኔታውን ለማጣራት ሲነሳ ብርሃኑ ተሰወረበት። ግቢው ውስጥ ቶዚ የተባለው የጀርመን ሼፐርድ ውሻቸው እንደዕብድ እየጮኸ ሽማግሌውን ሊጀንፊልድን ከእንቅልፉ ቀሰቀሰው። ነገሩ ምን እንደሆነ ለማጣራት ሽማግሊው ወጣ። በጎቹም ተሽብረው እርስ በራሳቸው ይጋጫሉ። የውሃ መጠጫ ገንዳቸው በትናንትናው ዝናብ ሞልቶ እንዳልነበረ ሁሉ አሁን እንደ አጥንት ደርቆ አገኘው።

ቶዚ እየሮጠና በፍርሃት እያላዘነ ሽማግሌው ስር ሲወሸቅ ሽማግሌው በሐሳብ ተውጦ ውሻውን እየደባበሰ አረጋጋው።

ልክ በዚህ ወቅት የቤቱ መብራት በሙሉ ድርግም ብሎ ጠፋ። ሽማግሌው ወደ ቤቱ ተመለሰና የመብራት ኃይል ኩባንያውን በስልክ ለመጠየቅ ሲሞክር ስልኩ የማይሠራ ሆኖ አገኘው። መብራቱ ለትንሽ ጊዜ ሳይጠፋ ቢቆይ ኖሮ አንዲት እጅግ በጣም የተዋበች ሴት ከመጋዘኑ ውስጥ ወጥታ ከቤቱ ማዶ ወዳለው ሜዳ ስትሄድ ማየት በቻለ ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ አራት

<u>ቡንዴሳን ዋልትሲቻፍት ጀኔቫ 1330 ሰዓት</u>

ሚኒስትሩ በስዊስ የመረጃ ድርጅት ሕንፃ አንድ ቢሮ ውስጥ ተቀምጠው የመረጃ ድርጅቱ ምክትል ዳሬክተር መልዕክቱን እንብቦ እስኪጨርስ ያዳምጡ ነበር። ትዕዛዝ አዘሉን ወረቀት ማኅደሩ ውስጥ አስቀምጦ ማኅደሩን መሳቢያ ውስጥ ከከተተ በኋላ መሳቢያውን ቆለፈው።

"ሐንስ ቤከርማንና ፍሪትዝ ማንደል።"

"እምን።"

"ይወገዱ!"

"ምን?"

"ይገደሉ! በአስቸኳይ!"

---



@BOOKALEM

"ቫምፒሮቻችሁን ከላውንደሬ ቤት ማውጣት አትርሳ! ይሆን ጊዜ ቤትህ አሁን የወለደችበት መስሏል" ትለዋለች። አያንዳንዱ ጥሪዋ ብቸኝነቱን የሚያቋቁመው አደረገበት። በሰርግ ዋዜማ ጥሪ አድርጋለት ነበር።

"ሮበርት በነገው ዕለት የማገባ መሆኑን ላሳውቅህ እፈልጋለሁ ።"

ትንፋሹ እያጠረው "ሱዛን......"ሲል ጀመረ።

"ምንቴን አፈቅረዋለሁ። እንተንም በጣም አፈቅርሃለሁ። እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ አፈቅርሃለሁ። ይህንን ፍጹም እንድትረሳው አልፈልግም።"

'ለዚህ ምን የሚሰጥ መልስ አለ?' ሲል አሰበ።

"ሮበርት ደህና ነህ?" አለችው ድምጹ ሲጠፋባት። "ሮበርት? ሮበርት አለህ?"

በራሱ አካላዊ ችግር ሲቀጣት አልፈለገም። "እባክሽ አንድ ውለታ ብቻ እንድትውይልኝ ልጠይቅሽ?"

"ምንም ነገር! የምችለውን ሁሉ!"

"እባክሽን ለሜንጫ ሽርሽራችሁ እኔ ወደ ወሰድኩሽ ሥፍራዎች እንዲወስድሽ አታድርጊ!" አለና ስልኩን ዘጋው።

ስልኩንም ዘጋና ጥንብር ብሎ ለመስከር ወደ ውጭ ወጣ። ይህ ከሆነ አንድ ዓመት ያለፈው ታሪክ ነበር። አሁን ሱዛን የሌላ ሰው ንብረት የመሆኗን ዕውነታ ለመቀበል ተገደደ። ባለፈው ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ ውስጥ መኖር አለበት። መሥራት የሚገባውም ሥራ አለ። አሁን ወቅቱ የምስከርቹን ስምና አድራሻ እንዲሁም ፎቶግራፍ የያዘውን ሊስሊ ማዘር ሼድን የመጨረሻው በሆነው ተልዕኮው የሚንጋገሪያው ጊዜ ነው።



@BOOKALEM

'መገልባት ፍጠሩ ባለአንድ እጅ ብቻ መሆን አለበት' ሲል አሰበ።

'መናልባት ፍጠሩ ባለአንድ እጅ ብቻ መሆን አለበት' ሲል አሰበ። 'ምናልባት ፍጠሩ ባለአንድ እጅ ብቻ መሆን አለበት' ሲል አሰበ።

"የምኖረው ከዚህ ሰው ጋር ነበር። ልብሶቼ በአጠቃላይ ውስጥ ስለሆኑ ገብቼ ለማው......"

የእሳት አደጋ ሠራተኛው አንገቱን አወዛወዘ። "ምንም የሚረባ ነገር የለም ጌታዬ። መኖሪያ አፓርተመንቱ ውስጥ ከአመድ በስተቀር የቀረ ነገር የለም።"

'ፎቶ ግራፎቼንና ብርቅዬውን የስም ዝርዝር ጨምሮ!' ሲል ሮበርት በምሬት አሰበ።

---

ዋሺንግተን ከተማ ደስቲን ቶርንቶን በሚስቱ አባት በዊላርድ ስተን ጽሕፈት ቤት ምቹ የመመገቢያ ክፍል ውስጥ ምሳ እየበላ ነበር። ደስቲን ቶርንቶን ተሸብሯል። ደስቲን ሁልጊዜ ኃያል አማቱ አጠገቡ ካለ እንደተሸበረ ነው።

ዊላርድ ስተን በደስታ ስሜት ውስጥ ነበር። "ትናንት ማታ ከፕሬዚዳንቱ ጋር እራት አብረን ተመግበናል። በዛን ወቅት በሥራህ በጣም እንደተደሰተ ነግሮኛል። በጣም ተደስቻለሁ ደስቲን!" አለ ዊላርድ ስተን።

"በጣም ግሩም ሥራ እያከናወንክ ነው። እኛን ከዘላኖቹ አደጋ ለመከላከል በጣም ግሩም እያደረክ ነው።"

"ዘላኖች?"

አዎን። ይህችን ታላቅ አገር በጉልበቶቿ ለማንበርከክ ጠላት ብቻ ሳይሆን አገራቸውንም የሚያገለግሉ እየመሰሉ ተግባራቸውን ማከናወን ያቃታቸውን፣ የሚሰጣቸውን ትዕዛዝ መፈፀም ያቃታቸውንም ጭምር ነው የምንከላከለው።

"ዘዋሪዎቹን?"

"ትክክል። ዘዋሪዎቹ መቀጣት አለባቸው።"

አንድ ሰው ወደ ምግብ ቤቱ ገባ። "ይቅርታ ሚስተር ስተን። የተከበሩት ሰዎች ደርሰዋል። እርስዎን እየጠየቁ ነው።"

"እሺ!" አለና ወደ ደስቲን ዞር ብሎ "ምሳህን ጨርስ። አንድ የምመለከተው በጣም ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ አለ። አንድ ቀን ልነግርህ እችል ይሆናል" አለው።



@BOOKALEM

ፕሮፌሰሩ ብስጭታቸውን ለመደበቅ እየሞከሩ......"ምናልባት መልሰህ ልታመጣው ትችላለህ? ለምን ካርድህን አትሰጠኝም? የበለጠ የማገኘው ጉዳይ ካለ ልደውልልህ እችላለሁ" አሉት።

"እንደም ካርድ የያዝኩ አይመስለኝም" እያለ ሮበርት ኪሶቹን ፈታተሻቸው።

"እዎን እኔም እንዳልያዝክ ገምቻለሁ!" አሉ ፕሮፌሰሩ በጣም ቀስ ብለው።

ኮማንደር ቤላሚ ለጄነራል ሐሊያርድ ስልክ ደወለ። ጄኔራል ሐሊያርድ ስልኩን አነሳና "እቤት ኮማንደር!" አሉት።

"የአዲሱ ምስክር ስም ፕሮፌሰር ስትግሪድት ነው። ፕላተን ስትራስ 5 ሙኒክ ውስጥ ይኖራል።"

"እመሰግናለሁ ኮማንደር። የጀርመንን ባለሥልጣናት ባስቸኳይ አሳውቃቸዋለሁ።"

ሮበርት ላገኘው የምችለው የመጨረሻው ምስክር ይህ ብቻ ነው ለማለት ጥቂት ነበር የቀረው። ግን አንድ የሆነ ነገር ያዘው። ሽንፈትን ማመን እጅግ ይጠላ ነበር። ግን የከትትሉ ፈለግ ቀዘቀዘበት። አንድ ቴክሳንና አንድ ቄስ። ቄሱ የመጡት ከሮም። በሚሊዩን ከሚቆጠሩ ቄሶች ውስጥ ለይቶ ማግኛ መንገድ የለውም። 'ምርጫ አለኝ' አለ ሮበርት። 'መመለስ ወይም ወደ ሮም ተጉዤ አንድ የመጨረሻ ሙከራ አደርጋለሁ' አለ።

---

ቡንዳሼር ፋሱንገሶት ዛሞት። (የሕገ መንግሥቱ የመከላከያ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት) በማዕከላዊ የበርሊን ከተማ ኑማርከር ጎዳና ላይ ይገኛል። ትልቅና ግራጫማ ቀለም ያለው በአካባቢው ካሉት ሕንፃዎች የሚለይ ነው። በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ የመሥሪያ ቤቱ ቺፍ ኢንስፔክተር ኦቶ ጆአኪም አንድ መልዕክት እያጠና ነበር። ሁለት ጊዜ በጥንቃቄ አነበበውና ከጠረጴዛው ላይ ቀይ ስልክ አነሳ።



@BOOKALEM

የአሪቬቶን አክሱተኛ ሆስፒታል ተረኛ ነርሶች መጠባበቂያ ዴስክ እንዲት መነኩሴ አልፋው ስትሄድ ከአኩሉ ሌሊት ጥቂት አለፍ ብሎ ነበር።

"ሲኞራ ፊሊፒንን ለማየት ነው የምትሄደው ብዬ እገምታለሁ" አለች ነርስ ቶማሲኖ።

"እርሷን ወይም ሽማግሌው ፊጋኖን ይሆናል!" አለች ሌላዋ ነርስ። ሁለቱም በመጨረሻው የሥራ ሰዓታቸው ላይ ነበሩ፡

መነኩሴቷ ዙሪያውን በቀስታ ተመለከተችና በቀጥታ ቄሱ የተኙበት ክፍል ውስጥ ገባች። ቄሱ ልክ ጸሎት ያደርጉ ይመስል እጆቻቸውን ደረታቸው ላይ አነባብረው በሰላም በእምነ ለጥ ብለው ተኝተዋል። የጨረቃዋ ብርሃን በቀጭኑ በተከፈተው መጋረጃ ውስጥ አልፋ ፊታቸው ላይ በማረፍ ወርቃማ ነጸብራቋን ጥላባቸዋለች።

መነኩሴቷ አንዲት ትንሽ ሳጥን ከረጅሙ ልብሷ ውስጥ አወጣችና በጥንቃቄ ከብርጭቆ የተሠራ የመጸለያ መቁጠሪያ አውጥታ በቄሱ እጆች ላይ አኖረችው። እንዱን የመቁጠሪያ ኳስ አውራ ጣታቸው ላይ ልክ በመቁጠር ላይ የነበሩ አስመስላ አስነካችው። ወዲያውኑ ከአውራ ጣታቸው ላይ ቀጭን የደም መስመር ወጣ። መነኩሴቷ ቀጥላ ከሳጥኑ ውስጥ አንድ ፈሳሽ የያዘ ትንሽ ብልቃጥ አወጣችና በዐይን ውስጥ ጠብታ በሚጨመርበት ዕቃ በመጠቀም ሦስት ጠብታዎች የተቆረጠው ጣታቸው ላይ ጨመረችበት።

አደገኛው ገዳይ መርዝ በደማቸው ውስጥ እስኪሰራጭ ድረስ በጣም ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነው የፈጀበት። ከዚያም መነኩሴቷ ሽማግሌው ቄስ አስከሬን ላይ አማተበችና ልክ እንደአመጣጧ ሳትታይ ሹልክ ብላ ወጣች።

አስቸኳይ መልክት

እጅግ በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

ሲፋር–ለ ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል

ምክትል ዳይሬክተር

በዐይኖች ብቻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

-5- አባ ፓትሮኒ ተወግደዋል

የመልዕክት መጨረሻ



@BOOKALEM

"እመሰግናለሁ።"

---

እስቶኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
የብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ለ–ዲ.ጂ.ኤች.ኪ.ው....
መረጃ ድርጅት ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
እርእስት– የፍርድ ቀን ዘመቻ
-7- ዊሊያም ማን–ፎርት ስሚዝ
የመልዕክት መጨረሻ

---

በዚያ ዕለት ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ የዊሊያም ማን የበር መጥሪያ ተደወለ። ማንም የሚጠብቀው ሰው ካለመኖሩም በላይ ቀጠሮ ያላስያዙ ጎብኝዎችን እጅግ ይጠላ ነበር። የቤት ጠባቂው ሥራውን ጨርሶ እርፏል። ሚስቱም ፎቅ ላይ መኝታ ቤት ተኝታለች። ዊሊያም እየተበሳጨ በሩን ከፈተ።

ጥቁር ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በሩ ላይ ቆመዋል።

"ዊሊያም ማን?"

"አዎን።"

አንደኛው የመታወቂያ ካርድ አውጥቶ እያሳየው "ከባንክ ካናዳ ነው የመጣነው። ወደ ውስጥ እንግባ?" አለው።

"ምንድነው የምትፈልጉት?"

"ግድ ካልሰጠህ ይህንን ጉዳይ እቤት ውስጥ ብንነጋገር ይሻላል።"

"በጣም ጥሩ!" አለና ሰዎቹን ወደ ውስጥ መራቸው።

"ቀደም ሲል ስዊዘርላንድ ውስጥ ነበርክ። አልነበርክም?"

ጥያቄው ከግምት ውጭ ሆነበት "ምን?"

"አንተ እዚያ በነበርክበት ጊዜ መዛግብትህን አስመርምረን ነበር። ሚስተር ማን! በባንክህ ውስጥ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ጉድለት እንዳለ አውቀሃል?"

ዊሊያም ማን ሁለቱን ሰዎች በፍርሃት ተመለከታቸው። "ምንድን ነው የምታወሩት? እነዚያን መዛግብት ራሴ ነኝ በየሳምንቱ የምመረምራቸው። አንዲት ሳንቲም እንኳ ጎድላ አታውቅም።"

"አንድ ሚሊዮን ዶላር ሚስተር ማን! ገንዘቡንም ለግል ጥቅምህ አባክነህዋል ብለን እናምናለን።"



@BOOKALEM

"እምን" አለ ማን። "ጸጸቴን ጽፌያለሁ። አሁን አትሄዱልኝም?"

"በግራ እጅህ እንደምትሠራ አየሁኝ።"

"ምን?"

"የግራ እጅ ተጠቃሚ ነህ።"

"እምን።"

"በዚህ አካባቢ ቀደም ሲል በርከት ያለ ወንጀል ተፈጽሟል። ይህንን ሽጉጥ ራስህን እንድትከላከልበት ልተውልህ ነው።"

ሽጉጥ ግራ እጁ ላይ ሲቀመጥለት ተሰማው። "ሽጉጥ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ታውቃለህ?"

"አላውቅም።"

"በጣም ቀላል ነው። ልክ እንደዚህ አድርግ......" አለና ሰውየው ሽጉጡን ወደ ዊሊያም ጆሮ ግንድ ቀና አደረገና ቃታውን ሳበው። የታፈነ ጩኸት ከድምጽ አልባው መሣሪያ ሲሰማ በደም የጨቀየው ወረቀት ደግሞ ወለሉ ላይ ወደቀ።

"ይኸው ነው። ደህና እደር ሚስተር ማን!" አለ ሌላው ሰውዬ።

እስቾኳይ መልዕክት

በጣም ከፍተኛ ምሥጢር

ሲ.ጂ.ኤች.ኪው ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል

የካናዳ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ምክትል ዳይሬክተር

ዐይኖች ብቻ

ግልባጭ የለውም

አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ

-7-ዊሊያም ማን. ፎርት ስሚዝ ተወግዷል

የመልዕክት መጨረሻ

---

## እሥረኛ ቀን

## ፎርት ስሚዝ ካናዳ

በማግስቱ ጠዋት የባንኩ መርማሪዎች ከባንኩ ሒሳብ ውስጥ አንድ ሚሊዮን ዶላር መጥፋቱን አስታወቁ። ፖሊስ የዊሊያም ማንን አሟሟት እራሱን በራሱ ማጥፋት ሲል መዘገበው። የጠፋው ገንዘብም ሳይገኝ ቀረ።



@BOOKALEM

የስዊስ ሕዝብ ቻሌት የሚላቸውን ዐይነት አነስተኛ መኖሪያ ቤት በተራራው ላይ ይኖረኛል። እናም ሁልጊዜ በሳጥን የተሞሉ ቼኮሌቶች ይኖሩኛል።"

ግሮምኮቭ በከባዱ እየተነፈሰ ከላይዋ ላይ ተነሳና "ዜምስኪይ! ተሪው ምንተ ነው!" አለው።

'ባል አገባና ልጆች ወልጄ በክረምቱ ወራት በአልፕስ ተራራዎች ላይ ለበረዶ ሸርተቴ ጨዋታ እንሄዳለን።'

ዜምስኪይ ተጋደመባት።

'በጣም ማራኪ የሆነ ሕይወት ይኖረኛል። ወደ ኋላ በፍጹም.....በፍጹም......'

ሰውየው ከመጀመሪያው የበለጠ እየጎዳት ነው።

'በጣም ውብ የአበባ ሥፍራ ባለው ፀጥተኛና ሰላማዊ እርሻ ላይ እንኖራለን.....።' እልጋ ሌላ ነገር ማሰቧን ቀጠለች።

ዜምስኪይ ጉዳዩን ጨርሶ ቆና አለና ወደ ባልደረባው ተመለከተ።

"ተደስታለች ብዬ አገምታለሁ!"

"ኢጆቹን ወደ እልጋ ላከና አንገቷን ጠምዝዞ ሰበረው።"

በማግስቱ ጠዋት የከተማው ጋዜጣ አንዲት ሴት የግዳጅ ግብረ ሥጋ ከተፈፀመባት በኋላ ተገድላ መገኘቷን የሚያወሳ ዘገባ ይዞ ወጣ። ባለሥልጣናት "በምሽት ሴቶች ብቻቸውን ወደ መናፈሻ ሥፍራ መሄድ በጣም አደገኛ ነው!" ሲሉ አስጠነቀቁ።

---

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ጂ.አር.ዩ. ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-ፄ-እልጋ ሮማንቻንኮ–ኪየቭ ተወግዳለች
የመልዕክት መጨረሻ



@BOOKALEM

"ፖል።"

"መጠጥ ለምን አልገዛልህም ፖል?"

"በጣም አመሰግናለሁ።"

"ለምሽቱ የተለየ እቅድ አለህ?"

"ይህ የአንተ ጉዳይ ነው።"

"ምሽቱን ከኔ ጋር ብታሳልፍስ?"

"አስደሳች ይመስላል።"

"በምን ያህል ገንዘብ ነው የምንነጋገረው?"

"ስለወደዱኩህ ሁለት መቶ ዶላር ብቻ ይበቃኛል።"

"ምን ያህል ተገቢ ይመስላል?"

"ፈጽሞ አታገኝበትም።"

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ፖል ኬቨንን በጀፈርሰን ጎዳና ወደሚገኝ አንድ አሮጌ የአፓርታማ ሕንፃ እየመራ ወሰደው። ሦስተኛው ፎቅ ላይ የሚገኝ አንድ አነስተኛ ከፍል ውስጥ እንደገቡ ፓርከር ዙሪያውን ተመለከተ። "ብዙም አጥጋቢ አይደለም። ነው? የሆቴል ከፍል ሳይሻል አይቀርም።"

ፖል ሳቅ አለና......"እዚህ ምሥጢራዊ የሆነ ሥፍራ ከመሆኑም ባሻገር የምንፈልገው አልጋውን ብቻ ነው" አለ።

"ትክክል ነህ። ለምን ልብስህን አታወልቅም? የገዛሁትን ለማየት እሻለሁ።"

"በእርግጥ!" አለና ፖል ማወላለቅ ጀመረ። ግሩም የሆነ ሰውነት ነበረው።

"በል አንተም ቶሎ አወላልቅ። እፈልግሃለሁ!" ሲል ፖል ሹክ አለ። "ከንፈር ነው ወይንስ ጭን የምትፈልገው?" ሲል ፖል ጠየቀ።

"አጥፊቲሽ ብናደርገውስ?"

"መታጠቢያ ቤት ልግባ። ቶሎ እመለሳለሁ" አለ ፖል።

ፓርከር የሚቀጥለውን መጪ ደስታ እያሰበ ራቁቱን ተጋደመ። ባልደረባው ከመታጠቢያ ቤት ወጥቶ መኝታውን ሲጠጋ ተሰማ።

እጆቹን ዘረጋና......"ናልኝ ፖል!" አለው።

"መጣሁልህ!"

ፓርከር ሥሲታም ጩቤ ደረቱን በጥርቆት ሲገባ የፍንዳታ ዐይነት ሕመም ተሰማው። ዐይኖቹን ከፈታቸውና እያቃሰተ ወደ ላይ ተመለከተ። "አምላኬ ምንድነው......?"

ፖል እየለባበሰ ነበር። "ስለገንዘቡ አትጨነቅ በምክር ቤቱ ሒሳብ ነው።"



@BOOKALEM

ልትችሁን የማትረሱት ተዕይንት ነው።' እንደገና ከማሪካ ጋር አልጋ ውስጥ ነበር። በመላ ሰውነቱ ላይ እየተሳበች በምላሷና በእጆቿ ስትዳስሰው እጁን ይሰማዋል። እሱም ወደ እርሷ ቀስ ብሎ እጁን ሰደደ። አንድ ቀዝቃዛና የሚለሰልስ ነገር እጁ ላይ ተሰማው። ከእንቅልፍ ሰመመኑ ነቃና ዐይኖቹን ገለጣቸው። ወዲያው ጩኸቱን አቀለጠው። ልክ በዚያች ቅጽበት መርዘኛው ኮብራ ጥቃቱን ሰነዘረ።

ጠዋት አስከሬኑ ሲገኝ መርዘኛው እባብ የነበረበት ጎጆ ግን ባዶ ነበር።

---

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ኤችአርኪው. የሁንጋሪያ መረጃ ድርጅት
ለ–ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርእስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
-10-ላስሎ ቡሽፈኪት -ሶፐሮን- ተወግዷል
የመጨረሻ መልዕክት

---

ጀነራል ሒሊያርድ በቀዩ ስልክ ጥሪ አደረገ። "ጃኑስ! የመጨረሻውን ሪፖርት ከኮማንደር ቤላሚ ተቀብያለሁ። የመጨረሻውን ምስክር ፈልጎ ያገኘ ሲሆን በሙሉ አስፈላጊው የጥንቃቄ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።"

"እጅግ በጣም ጥሩ። ሌሎቹንም አሳውቃቸዋለሁ። በቀሪው ፕላናችን መሠረት ወዲያው አስፈላጊውን ሥራ እንድትጀምር እፈልጋለሁ ።"

"ወዲያውኑ ጌታዬ!"

አስቸኳይ መልዕክት
በጣም ከፍተኛ ምሥጢር
ኤንኤስኤ (ብሔራዊ ፀጥታ ወኪል)
ለ–ሲ.ጆ.ኤችአር.ኪው
ለ– ቢ.ኤፍ.ቢ.
ለ–ኤም.አይ.6
ለ– ሲ.አይ.ኤ
ለ– ኮምሲክ
ለ–ዲ.ሲ.አይ
ለ– ሲፋር
ምክትል ዳይሬክተር
ዐይኖች ብቻ
ግልባጭ የለውም
አርስስት–የፍርድ ቀን ዘመቻ
11-ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ–ይወገድ!
የመልዕክት መጨረሻ

---



@BOOKALEM

"እዚህ ሮም ውስጥ ነኝ። ከዚህ የተረገመ ከተማህ ለመውጣት የምትችል አልመሰለኝም።"

ለጥቂት ደቂቃዎች በሐሳብ የተሞላ የፀጥታ ጊዜ አለፈ። "እንተን ለመርዳት ምን የማደርገው ነገር አለ?"

"ልንነጋገር ወደምንችልበት አስተማማኝ ቤት ውሰደኝ። ከዚያም እንዴት ለመውጣት እንደምችል እቅድ እወጣለሁ። ይህንን ማመቻቸት ትችላለህ?"

"እዎን ግን በጣም መጠንቀቅ አለብህ። እኔ እራሴ መጥቼ እወስድሃለሁ።"

ሮበርት በረዥሙ በእፎይታ ተነፈሰ። "እመሰግናለሁ ፍራንሲስኮ። በእውነት አደንቅሃለሁ።"

"እናንተ አሜሪካዊያን እንደምትሉት......"ብድር አለብህ!"፣ አሁን የት ነው ያለህው?"

"ትሬስቴቬር ውስጥ ሲዶ ቡና ቤት።"

"እዚያው ጠብቀኝ። በአንድ ሰዓት ውስጥ አገኝሃለሁ።"

"አመሰግናለሁ አሚኮ!" አለና ሮበርት ስልኩን አስቀመጠ። 'በጣም ረዥም ሰዓት ሊሆን ነው አለ በሐሳቡ።'

ከሠላሳ ደቂቃዎች በኋላ ሁለት ምልክት የሌላቸው መኪናዎች ከሲዶ ቡና ቤት አሥር ያርድ ያህል ራቅ ብለው ቆሙ። እያንዳንዱ መኪና ውስጥ አራት አራት ሰዎች ሲኖሩ በሙሉ አውቶማቲክ መሣሪያዎች ታጥቀዋል።

ኮሎኔል ቄሳር ከመኪናው ውስጥ ወጣና......"ይህንን ጉዳይ በፀጥታ እንፈጽመው፣ ማንም ሰው እንዲጎዳ ማድረግ የለብንም" አለ። "እልዳነቴ እልዳይትሮ ሱቪቶ!" ግማሾቹ የሕንፃውን ጀርባ ለመሸፈን ዞሩ።

ኮማንደር ሮበርት ቤላሚ ከመንገዱ ባሻገር የአንድ ሕንፃ የመጨረሻ ጣሪያ ላይ ሆኖ ሰዎቹ መሣሪያቸውን ደግነው ያለ የሌለ ጥይታቸውን ቡና ቤቱ ላይ ሲያዘንቡበት ተመለከተ።

'ጥሩ እናንተ ዱቃሎች! ጨዋታውን በናንተ ሀይነት መንገድ እንጫወተዋለን' አለ በሐሳቡ በይቅርታ የለሽነት።



@BOOKALEM

"በትክክል።"

ጄኔራል ሐሊያርድ ከንፈሩን መጠጠና....."ይህ የሚጎዳ ጉዳይ ነው። ራሳችንን ማጋለጥ አንችልም!" አለ።

"ምንን ማድረግ የለብንም። በአደንዛዥ ዕፅ ንግድ ከስ እንደሚፈለግ አድርገን መግለጫ እናወጣበታለን። በዚህ ዐይነት መንገድ ኢንተርፖልና የመላው አውሮፓ የፖሊስ ኃይል እኛ እጃችንን ሳናስነካ ከኋላው እንዲሰማራበት ለማድረግ እንችላለን።"

ጄኔራል ሐሊያርድ በዚህ ሐሳብ ላይ ለጥቂት ጊዜ ሲያስብ ቆየና "ጥሩ! ሐሳቡን ወድጀዋለሁ" አለ።

"በጣም ጥሩ! እኔም ወደ ሮም ሄጄ ራሴ አደኑን በበላይነት እመራለሁ" አለ ኮለኔል ጆንሰን።

ኮሎኔል ጆንሰን ወደ ቢሮው እንደተመለሰ በሐሳብ ባሕር ሰጠመ። አደገኛ የሆነ የድብብቆሽ ጨዋታ ነበር በመጫወት ላይ ያለው። አደገኛነቱ የማያጠያይቅ ነው። ኮማንደር ሮበርት ቤላሚን መፈለግ አለበት።

## ምዕራፍ ሠላሳ ስድስት

ሮበርት ስልኩ ደግሞ ደጋግሞ ሲጮህ ይሰማዋል። አሁን ዋሺንግተን ውስጥ ከማለዳው አሥራ ሁለት ሰዓት ነው። 'ሽማግሌውን ሁልጊዜ እንደቀሰቀስኩት ነው' ሲል አሰበ።

አድሚራሉ በስድስተኛው ጥሪ ስልኩን አነሳ። "ሄሎ....."

"አድሚራል እኔ......"

"ሮበርት ምን?"

"ምንም ነገር አይናገሩ አድሚራል። ምናልባት ስልከዎ የማዳመጫ መሣሪያ ተደርጎበት ይሆናል። በፍጥነት እናገራለሁ። ስለኔ የሚነገረውን ነገር ሁሉ በፍጹም እንዳያምኑ። ምን በመደረግና በመከናወን ላይ እንዳለ እንዲያጣሩልኝ እፈልጋለሁ ። ዘግይቶ ዕርዳታዎን ሳልፈልግ አልቀርም።"

"ማድረግ የምችለውን ሁሉ ሮበርት!" አለ አድራሚሉ።

"አውቃለሁ። ቆይቼ እደውላለሁ" አለና ሮበርት ስልኩን አስቀመጠው። ለአቅጣጫ መጠቆሚያ መሣሪያ ምንም ጊዜ አልሰጠም ነበር። አንድ ሰማያዊ ቀለም ያላት ፊያት መኪና ወደ ቡና ቤቱ ስትመጣ ተመለከተ። መሪውን የያዘችው ፒየር ነበረች።

"ወዲያኛው ወንበር ላይ እለፊ! እኔ እሽከረክራለሁ" አላት ሮበርት። ፒየር ቦታውን ስትለቅለት እሱ መሪውን ያዘ።

"አሁን ወደ ቬኒስ ነው የምንጓዘው?" ስትል ጠየቀችው ፒየር።



@BOOKALEM

# ምዕራፍ አርባ አራት

የስልክ ጥሪው ለኮሎኔል ቁሳር ተላለፈለት። "አዎን" አለው ጁሴፔን። "የኛን ሰው ይመስላል። በጥንቃቄ አዳምጠኝ። በጣም አደገኛ የሆነ ሰው ነው። ስለዚህ ልክ እንደነገርኩህ ማድርግ አለብህ። ገባህ?"

"እሺን ጌታዬ።"

"አሁን የት ነው ያለህው?"

"ወደ ሴቪታቬቺያ በሚወስደው ጎዳና የካሚዎን ነዳጅ ማደያ ላይ።"

"እሱ አሁን የካሚዎንህ መጫኛ ላይ ነው ያለው?"

"አዎን!" አለ ጁሴፔ። ቃለ ምልልሱ አስጨነቀው። 'ምናልባት አርፌ ሥራዬን ብሠራ ይሻል ነበር።'

"ሰውየው እንዲጠራጠር የሚያደርገው ምንም ነገር አታድርግ። ወደ ካሚዎንህ ተመለስና ወደ ሲቪታቬቺያ መንዳትህን ቀጥል። የካሚዎንህን የሰሌዳ ቁጥርና የመኪናውን ቀለም ንገረኝ።"

ጁሴፔ ነገረው።

"መልካም! አስፈላጊውን ርምጃ እንወስዳለን። አሁን ተንቀሳቀስ!" ኮሎኔል ቁሳር ወደ ኮሎኔል ጆንሰን ዞረና ራሱን ነቀነቀ። "አገኘነው! የመንገድ መሰናክል እንዲደረግ አዛለሁ። በሠላሳ ደቂቃዎች ውስጥ እቦታው ላይ በሄሎኮፕተር መድረስ እንችላለን።"

"እንሂድ።"

ጁሴፔ ስልኩን ከዘጋ በኋላ ላቡን እየጠራረገ ወደ ጭነት መኪናው ተመለሰ። 'ሙቼም ተኩስ እንደማይከፈት ተስፋ አደርጋለሁ። ማሪያ ትገለኛለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሽልማቱ ብዙ ከሆነ......'ጋቢና ገባና በቀጥታ ወደ ሲቢታቬቺያ ማሽከርከር ጀመረ።

ከሠላሳ አምስት ደቂቃዎች በኋላ ጁሴፔ ከአናቱ በላይ የሄሊኮፕተር ድምጽ ተሰማውና ቀና ብሎ ተመለከተ። የፖሊስ አርማ ነበረበት። ከፊት ለፊቱ ደግሞ ራቅ ብሎ ሁለት የፖሊስ መኪኖች መንገዱን ዘግተው ቆመዋል። ሄሊኮፕተሩ ከመንገድ ጠርዝ ላይ ሲያርፍ ኮሎኔል ፍራንክ ጆንሰን እና ኮሎኔል ቁሳር ከሄሊኮፕተሩ ወረዱ።



@BOOKALEM

"ምልክቱም የለም ኮማንደር!" አለ አንዱ ባሕረኛ።

"እርግጠኛ ነህ?" አለ ኮማንደሩ።

"ፍጹም እርግጠኛ ነኝ ጌታዬ!" መርከቧ በረንዳ ላይ ምንም ተሳፍሪ የሌለ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱን ሠራተኛም ተመልክተናል።

ኮማንደሩ ባለበት ሥፍራ ተሸብሮ ቆመ። የበላይ አለቆቹ በጣም ከፍተኛ የሆነ ስህተት ሠርተዋል። ወደ ሞንቴ ስዞንና ካፒቴን ሲምፕሰን ፊቱን አዞረና....."ይቅርታ መጠየቅ ይገባኛል። ስላስቸገርናችሁ እጅግ በጣም አዝናለሁ። አሁን መርከባችሁን እንለቃለን!" አለና ለመሄድ ፊቱን አዞረ።

"ኮማንደር" አለው ሞንቴ።

"አቤት"

"እናንተ ምትፈልጉት ሰው ከሠላሳ ደቂቃዎች በፊት በዓሣ ማጥመጃ ጀልባ ሄዷል። እሱን ለመያዝ ምንም ችግር አይገጥማችሁም።"

ከአምስት ደቂቃ በኋላ የጦር መርከቧ ስትርሞቦሊ ወደ ማርሴ አቅጣጫ ትበር ጀመር። ሊውተናንት ኮማንደሩ የሚደሰትበት ብዙ ምክንያት ነበረው። ኮማንደር ሮበርት ቤላሚን ግማሹ የዓለም መንግሥታት እያሳደዱት ሲሆን የሚያገኘው ግን እሱ ነው። 'ግሩም የሆነ የማዕረግ ዕድገት እኛለሁ' አለ በሐሳቡ።

ከመርከቧ ድልድይ ላይ ባሕረኛው መኮንን ተጣራ። "ኮማንደር እባክህን አንድ ጊዜ ወደዚህ ብትመጣ።"

'ዓሣ አጥማጁን ጀልባ አገኘት ማለት ነው?' ኮማንደሩ እየተጣደፈ ሄደ።

"ይመልከቱ ጌታዬ!"

ኮማንደሩ እንዴ ብቻ ሁኔታውን ተመለከተና ልቡ ቀለጠችበት። ከፊት ለፊቱ ራቅ ብሎ አጠቃላዩ የማርሴ ዓሣ አጥማጅ ጀልባዎች ባሕሩን እንደአሸን ሸፍነውታል። ከነሱ ውስጥ ደግሞ በመቶ የሚቆጠሩት አንድ ዐይነት ሲሆኑ ወደ ወደብ በመመለስ ላይ ነበሩ። ኮማንደር ቤላሚ የተሳፈረባትን ጀልባ ለማወቅ በዓለም ላይ ምንም ዐይነት ዘዴ ለም።



@BOOKALEM

## ምዕራፍ ሃምሳ

ከምድር እጅግ በጣም ከፍ ብላ በምትንሳፈፈው እናት የጠፈር መንኮራኩር ውስጥ ከፍተኛ ደስታ ተፈጠረ። በመቆጣጠሪያ መሣሪያዎቹ ላይ ያሉት መብራቶች በሙሉ አረንጓዴ ማብራት ጀመሩ።

"አገኘናት!"

"አሁን መፍጠን አለብን።"

ግዙፏ የጠፈር መንኮራኩር እጅግ በጣም ወደ ታች እርቃ ወደምትገኘው መሬት ተምዘገዘገች።



@BOOKALEM

"እምን ምንም ጉዳት አናደርስባችሁም!" አለችና እጇን ወደ ሦስቱ ሰዎች ዘረጋች። ለተወሰነ ግዜ ምንም የተፈጠረ ነገር አልነበረም። ከጥቂት ሰኮንዶች በኋላ ግን ሌሎቹ እየተመለከቱ ሦስቱ ሰዎች በደነዘዘ ሕሊናቸው ወደ ጠፈር መንኮራኩሯ መሄድ ጀመሩ።

"አይሆንም! አለና አድሚራል ዊታከር እሪታውን አቀለጠው። ሦስቱም መንኮራኩሯ ውስጥ ገብተው እስኪሰወሩ ድረስ እሪ... እያሉ ነበር።"

ነጭ ልብስ የለበሰችው ሴት ወደ ሌሎቹ ዞወር አለች። "ምንም ዐይነት ጉዳት አይደርስባቸውም። ብዙ የሚማሩት ነገር ይኖራል። ትምሕርታቸውን ሲጨርሱ ወደዚህ እንዲመለሱ ይደረጋል።" ሱዛን ሮበርትን ጠበቅ አድርጋ ይዛው ነበር።

"ሮበርት! ሰዎች ይህችን የምትኖሩባትን ፕላኔት መግደል እንዲያቆሙ ንገራቸው አስረዳቸው!"

"እኔ አንድ ሰው ብቻ ነኝ።"

"ያንተ ዐይነት በሺህ የሚቆጠሩ አሉ። በየዕለቱም ቁጥራችሁ እየጨመረ ነው። አንድ ቀን የናንተን ዐይነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ይኖሩና በአንድ ድምጽ መናገር ትችላላችሁ። ይህንን ታደርጋለህ?"

"እሞክራለሁ! እሞክራለሁ።" አላት ደገመና።

"አሁን መሄዳችን ነው። ነገር ግን እናንተን መመልከታችንን አናቋርጥም። እናም ተመልሰን እንመጣለን።"

ባለነጭ ልብሷ ሴት ፊቷን አዞረችና መንኮራኩሯ ውስጥ ገባች። በውስጡ ያሉት መብራቶች ሰማዩን እስኪያበሩት ድረስ እጅግ በጣም ብሩህ እየሆኑ መጡ። እናም በድንገት ያላንዳች ማስጠንቀቂያ ግዙፏ እናት የጠፈር መንኮራኩር በግልገሎቹ በራሪ መንኮራኩሮች ተከታይነት ወደ ሰማይ መጠቁና ከዐይን ተሰወሩ።

'ሰዎች ይህችን ፕላኔት እንዳይገድሏት ንገራቸው! ትክክል!› አለ ሮበርት በሐሳቡ። 'ካሁን በኋላ በቀሪው የሕይወት ዘመኔ ምን እንደምሠራ አውቃለሁ!' ሱዛንን ተመለከተና ፈገግ አለ።

ጆማሬው!



@BOOKALEM

ውስጥ እስካለሁ ድረስ ስለነርሱ ለመወያየት ብቃት አለኝ ብዬ አምናለሁ። እንደዚሁም ደግሞ በ1951 ዓ.ም በምድረ አውሮፓ ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ በተዋጊ የበረራ ሠልፍ ገብተው የተለያየ መጠን ያላቸውን መንኮራኩሮች ለሁለት ቀናት ያደረጉትን በርካታ በረራ የማየት ዕድል አጋጥሞኛል። በዚያን ጊዜ የኛ ተዋጊ ጄቶች ሊደርሱ ከሚችሉበት ከፍታ እጅግ በጣም ርቀው (ከፍ ብለው) ነበር የሚበሩት።

ከዚህም በማያያዝ ለማመልከት የምፈልገው በርካታ ጠፈርተኞች የዩ.ቢ.ኢን ጉዳይ በተመለከተ ለመወያየት ወይም ለመናገር በጣም ዝግተኞች ናቸው። ምክንያቱም በርካታ የሆኑ ሰዎች በግድ የለሽነት የማታለያ ታሪኮችንና የሐሰት ሰነዶችን በመሸጥ ስማቸውንና ዝናቸውን ያለማወላወል ስለሚያጠፉባቸው ነው። የ ያ.ቢ.ኢን ጉዳይ በተመለከተ ቀጣይ ተሳትፎ ያላቸው ጥቂት ጠፈርተኞች ሥራቸውን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማከናወን አለባቸው። በዩ.ቢ.ኢ. መኖር የምናምን እና ያ.ቢ.እዎችን መሬት ላይ ወይም ከአውሮፕላን ላይ የማየት ዕድል ያጋጠመን በርካታ ሰዎች አለን። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይህንን ፕሮጀክት ለማንቀሳቀስ ከተስማማ ምናልባት በርካታ ብቃት ያላቸው ሰዎች ፊት ለፊት ቀርበው በጉዳዩ ላይ ሊገኝ የሚችል ማስተማመኛ እገዛና መረጃ ሊለግሱ ይችላሉ።

በቅርቡ ላይዎት እሞክራለሁ።

በእውነት

ኤል ጎርደን ኩፐር

ኮሎኔል ዩ.ኤስ ኤር ፎርስ ጠፈርተኛ።

በኣብዓለም በቴሌግራም ያቀረበው መጽሐፍ
@BOOKALEM



@BOOKALEM



በስዊስ የአልፕስ ተራራ ላይ አንድ የአየር ንብረት መመርመሪያ ባሉን ተከስክሶ ተገኘ፡፡ እዚህ ላይ መላው ዓለም ከዚህ በፊት አይቶትም ሰምቶትም የማያውቀው ቅዠት ተጀመረ...!

እጅግ በጣም አስደንጋጭና አስፈሪ የሆነ ከፍተኛ ምስጢር በዓይናቸው የተመለከቱ አሥር የተለያዩ አገር ዜጎችን አድኖ እንዲይዝ ኮማንደር ቤላሚ ተመረጠ፡፡

ግዳጁን በመወጣት ላይ እንዳለ የመላው ዓለም መረጃ ድርጅቶች እሱን በማደን ላይ መሆናቸው ይሰማው ጀመር፡፡ ግን ለምን...?

እንደገና ኤዲት ተደረጎ ለ12ኛ ጊዜ የታተመ፡፡ የሲዲኒ ሼልደን የመጨረሻው ምርጥ መጽሐፍ!!

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ
0113 691933

121.50 ብር

@BOOKALEM